# መኢአድና መጪው ምርጫ!!!

(ሕዝቂያስ ፍቅሬ)

መቼም ስለምርጫ ሲታሰብ የዘጠና ሰባቱን ምርጫ እና የአጋዚን የጅምላ ጭፍጨፋ በሕሊናው የማያሳብ ኢትዮጵያዊ ያለ አይመስለኝም። “በዚህም ወቅት የኢያሪኮ የጨኸት ውርስ የነበረውን የአዲስ አበባውን ዋይታና ለቅሶ መቼም የማያስታውስ ሰው ያለ አይመስለኝም”። ስንቱ በአጋዚ ጥይት ተበላ?! አዛውንቱ፤አሮጊቱ፤ጎልማሳው፤ወጣቱ፤ሕፃኑ፤ እረ ስንቱ ቤቱ እና የአዲስ አበባ ጉድጓዶች ይቁጠሩት። ሚስት በባሏ ፊት፤ ባል በሚስት ፊት በአጋዚ ጥይት ተበላ።
ይሁን እንጂ ያለፈው አልፏል። ነገርን እየመላለሱ ቢቆዝሙት ጥላቻን በጭንቅላት እንዲሞላ ማድረግ እንጂ ምንም ፋይዳ ሲሰጥ አይታይም።

ይሁን እንጂ ለሚቀጥለው ምርጫ እንደዛ አይነቱ ነገር ዳግም እንዳይከሰት ምን አይነት ዋስትና አለ? መቼም ወያኔን ያመነ ጉም የዘገነ አይደለም የሚባለው ከነ ተረቱ። ይልቅስ ተቃዋሚዎች በዚህ ጉዳይ ላይ የአህምሮዋቸውን ጡንቻ ቢያፍታቱት መልካም ይመስለኛል። አበው እንዲህ ብለው የለም “በዕድሜህ ዕወቅበት ሰርተህ ክበርበት” አዎ የተቃዋሚ መሪዎች የእናቴ መቀነት አደናቀፈኝ ሳይመጣ ካሁኑ ግዜያቸውን ቢጠቀሙበት መልካም መስሎ ነው የሚታየኝ።

ዛሬ ትኩረቴን የሳበኝ ነገር የተከበሩ የኢንጅነር ሀይሉ ቃለምልልስ ከዋልታ ኢንፎርሜሽን ጋር ያደረጉት ነው። ከቀናቶች በፊት በኢንጅነሩ ላይ አንዳንድ ትችቶችን እሰማ ስለነበር ነው። ለነገሩ በሳቸው ቃለምልልስ ላይ እኔም በከፊልም ቢሆን አልረካሁም ነበር። ቢሆንም ቅሉ ዋልታዎች ቃለምልልሱን በተዛባ መልክ ኢንጅነሩን ሊያስወቅስ በሚችል መልኩ ነበር በድህረ ገፃቸው ላይ ያቀረቡት። ይሁን እንጂ ኢንጅነሩ ከቀናቶች በሁዋላ መግለጫ በማውጣት ማስተባበያ ሰጥተውበታል።
“እንዳባባላቸውም ዋልታ በተዛባ መልክ እንዳቀረበው እና ደጋፊዎችን ውዥንብር ውስጥ ለመክተት ታስቦ የተደረገ መሆኑን በግልፅ አስቀምጠዋል”። መግለጫው ኢንጅነሩን ቢያስመሰግናቸውም መግለጫው ዘግይቷል ባይ ነኝ። ኢንጅነሩ ወደፊት መረዳት አለባቸው ብዬ የማስበው እንደዚህ አይነቱ ጉዳይ ሲገጥማቸው የመልስ ምት ቶሎ መስጠት አለባቸው በማለት ነው።

በቃለ ምልልሱም ላይ ኢንጅነር ሀይሉ እንዳስረዱት ቅድመ ሁኔታዎች ከተሙዋሉ ለምርጫ እንቀርባለን በማለት ነው። አበው ምን ነበር ያሉት፤ “ሰማይ አይታረስ እርኩስ አይቀደስ” ነበር ያሉት፤ መቼም ይሞክሩት የሚቻል ከሆነ በእርግጥ ይቻላል የማይቻል ነገር የለም የኢትዮጵያ ህዝብ ሁሌም አሸናፊ ነው። ነገር ግን እንደባለፈው ወያኔ ግዜ እንዳይገዛባቸው ስጋቴ ነው። ጥንቃቄም ማድረግ እንዳለባቸው ከወዲሁ ሊያስቡበት ይገባል እላለሁኝ።

**እበላ ብዬ ተበላሁ፤ ምነው ሳልበላ በቀረሁ፤ ከመከሰቱ በፊት፤**

የተከበሩ ኢንጅነር ሀይሉ ከባለስልጣኖቻቸው ጋር ሆነው ስለመጪው ምርጫ ሌት ተቀን ሊመክሩበት ይገባል። እውነቴን ነው የምለው ጉዞው በማስተዋል ከሆነ እና በቁርጠኝነት ከሆነ ሁላችንም እንደምናውቀው የወያኔ መንግስት ብል በልቶት የጨረሰው እና እንኩዋንስ ሰው ገፍትሮት አይደለም በራሱ ሊወድቅ አንድ ሀሙስ የቀረው መንግስት ነው። እና እዬንን በመገንዘብ የመኢአድ አመራሮች ዳግመኛ  በወያኔ ላለመታለል ከፍተኛ ጥበብ የተሞላበት ስራ ማከናወን አለባቸው የሚልም ግምት አለኝ። ለዛም እገዛ እንዲረዳቸው ደጋፊዎቻቸውን በተቻላቸው መጠን አንድ ለማድረግ እና ደጋፊንም ለማብዛት ለመሞከር መስዋእትነት መክፈል አለባቸው። ይህ በእንዲህ እያለ ኢንጅነሩ በተቻላቸው መጠን ልዩነት እንዳይሰፋ በሌሎች የተቃዋሚ ቡድኖችም ላይ ምንም አይነት የተቃዎሞ አስተያየት እንዳይሰጡ አስተያየቴን ጃባ እላቸዋለሁኝ። በሌላው ላይ አስተያየት መስጠቱ ነው ሰውን እያከረረ እንዲመጣ እና መከፋፈልን እንዲመጣ ያደረገው። መቼም ሰው ካለፈው ስህተቱ ካልታረመ፤ መቼስ ማልጎደኒ ነው ያለው አያቴ፤ ምንም ማድረግ አይቻልም ልቦና እስኪመጣ ድረስ ወደላይ አንጋጦ አምላክን መለመን ነው። አሁንስ አምላክም የእኛ አቤቱታ በዝቶበት ነው መሰለኝ ጆሮ ዳባ ብሏል። ምን እኛ ላይ ያልጨከነ አለ። ብቻ አምላክ መቼም በልጆቹ ላይ እንደጨከነ አይቀርም። አንድ ቀን ፍቅሩን ያነበሸብሸን ይሆናል። ነገር ግን የአምላክን በረከት ለማግኘት እኛ መጀመሪያ መፋቀር አለብን። አምላክ ፍቅር ነውና።

**ካለጓደኛ መግፋት፤ ከንቱ ልፋት፤**

መቼም አለመታደል ሆኖ ተስማምቶ በአንድነት መስራት አልቻልንም። ይመስለኛል በልፋታችን ሁሉ ላይ በረከት እግዚአብሄርን ያሳጣን አንድነት ማጣታችን ይመስለኛል። ብቻ የማዝነው የኢትዮጵ ህዝብ በጠኔ ሲቆላ እያዩ እንወክልሀለን የሚሉት የፖለቲካ ፓርቲዎች እርስ በርስ ሲሻኮቱ ማየቱ እንዴት ልብን ያደማል። አባቶቻችን ወራሪ ጠላትን ሲመክቱ የነበረው “አመልህን በጉያ ስንቅህን በአህያ” በሚለው መፈክራቸው ነበር። ዛሬ ግን እያ ሁሉ የለም፤ አንድነት የሚሉት ቃል በራሱ ተሰርቆ ደደቢት በረሀ የገባ ነው አሁንስ መስሎ የታየኝ። ይልቅስ በኢትዮጵያነት ተደራጅተናል የሚሉ ሀይሎች ወደ አንድነት መምጣት እንኳን ባይችሉ እርስ በርስ ያላቸውን ሽኩቻ ወደጎን በማድረግ ትኩረታቸውን የጋራ ጠላታቸው ላይ በማድረግ ትግሉን ያፋፍሙት ዘንድ ልመናዬ ነው።

የሚገርመው ሽኩቻው ያለው በመሪዎቹ ብቻ ላይ ሳይሆን በደጋፊዎችም ላይ በሰፊው ይታያል። ለዚህም የመሪዎቹ ድክመት እና እኔን ካልነካኝ ምን አገባኝ በሚልው አመለካከታቸው ይመስለኛል። ህዝብን እወክላለሁ ከሚል መሪ ደግሞ እንደዚህ አይነቱ አመለካከት ባሰቸኳይ መታረም ይገባዋል። የተከበሩ ኢንጅነር ደጋፎዎችን አንድ የማድረጉ ስራ ላይም ትኩረትን ሰጥተው ቅራኔን ፈቺ ግብረ ሀይል በማቋቋም ያለውን የደጋፊዎችን የእርስ በርስ ሽኩቻ ባስቸኳይ እልባት ሊያበጁለት ይገባቸዋል።

ለሁላችንም ግልፅ እንደሆነው የሚቀጥለው ምርጫ እንደሚሳኤል እየተምዘገዘገ እየመጣ ነው። አቤት የቀኑ ፍጥነት፤ ለእኔ ምርጫ ዘጠና ሰባት ትናንትና መስሎ ነው የሚሰማኝ። ምርጫውንም አስከትሎ ደም አፍሻቾችንም ለፍርድ ሳናቀርብ እየው በእርስ በርስ ሽኩቻው ላይ ብቻ ተጠምደን አምስት አመት ልንደፍን ነው። ለዛም ሁላችንም ተጠያቂዎች ነን ብዬ ነው የማስበው። ምክንያቱም ሁላችንም በአጻያፊ ቃላቶች በመታገዝ ልዩነት እንዲሰፋ የበኩላችንን አስተዋፅኦ አድርገናል ብዬ ስለማስብ ነው። ውጤቱንም እንደምናየው ነው። አበወ ጨርሰውት ነበር እንዲህ በማለት “ ከአንድ ብርቱ ሁለት መድህኒቱ” ግን ምን ያደርጋል የአባቶቻችንን ምክር በአግባቡ መጠቀም ባለመቻላችን የሕዝባችንን **የጠኔ ዘመን** ማሳጠር አልቻልንም።

የሆነው ሆኖ ባለፈ ክረምት እቤት አየሰራም እንደሚባለው ሁሉ ስላለፈው ነገር ትተን ካለፈው ትምህርት ወስደን፤ በአንድነት ታጅበን፤ ልዩነታችንን በማጥበብ “እምዬ ምንይልክ እንዳሉት አመልን በጉያ ስንቅን በአሕያ” አደርገን የሕዛባችንን የጠኔ ዘመን ለማሳጠር ሽርጉዱን ከአሁኑ መጀመር አለብን እላለሁኝ።

## ኖሮ ኖሮ ከሞት፤ ዞሮ ዞሮ ከቤት

መቼም የተፈጥሮ እዳ ሆኖ፤ ሞት የማይቀር እዳ ነው። ሁሉም ሞቷል። እምዬ ምንይልክም፤ ቴዎድሮስም፤ ዮሀንስም፤ ጃንሆይም፤ በላይም፤ እረ ስንቱ ተዘርዝሮ ያልቃል። ሁሉም ሞቷል። ዛሬማ በኢትዮጵያ ላይ ሰው ብቻ ሳይሆን አገርም እየሞተ ነው። እረ የወንድ ያለህ የምንልበት ዘመን ላይ ደርሰናል። የድሮ አባቶቻችን አሟሟት እና የእኛ አሟሟት ለየቅል ነው። እነሱ በጀግንነት ሲሞቱ እኛ ደግሞ በፍራቻ፤ አቤት ሰው ለማይቀረው ሞት እንዴት በፍራቻ ይሞታል? ይታለስ በደም የወረስነው ጀግንነት? መቼም ዘመነ ግርምቢጥ ላይ የደረስን መስሎ ነው የሚሰማኝ።

መቼም ይህንን ስል በጅምላው ሁሉንም እንዳላልኩ ላሰምርበት እወዳለሁኝ። **ሽብሬ ደሳለኝ** የጀግና ሞት ሞታ አሳይታናለች። **እረ ምን ሽብሬ ብቻ መሪያችን ብርቱካን ሚደክሳስ ሞት ምናባቱ ብላ ሞትን ሳትፈራ ሰላምን ስለሰበከች ብቻ በቃልቲ እየማቀቀች ኤደለምን?** እኛም በፍራቻ ተሸብበን የቡርትዬን መታሰር ጆሮ ዳባ ብለነው የለምን? ብቻ ለሁሉም ታሪክ ይፍረደው። ይልቅስ ወገኖቼ ታሪክ ሰርተን እንሙት። የሰዉ መሞት ሳያንሰን እምዬ ኢትዮጵያም እየሞተች ነው። እረ የሀገር ያለህ ዝምታው ይፈታ?! አገራችንን ከጥፋት እንታደጋት?!

ይህ በእንዲህ እያለ ወደማጠቃለያው ስሄድ የፓለቲካ መሪዎችም ከፍራቻ ወጥተው ኢትዮጵያን ከገባችበት ወጥመድ ለማውጣት ህዝባቸውን ያለምንም ፍራቻ ያንቀሳቅሱት ዝንድ ምክሬ ነው። ለዚህም መኢአድ እና UDJ ዋነኛውን ስፍራ ይይዛሉ የሚል እምነት አለኝ። በሚቀጥለው ምርጫ እነኚህ ሁለቱ ፓርቲዎች ተዋህደው መስራት ባይችሉ እንኳን ልዩነታቸውን በጉያቸው ይዘው በልዩነታቸው ተከባብረው ህዝባቸውን በየቅላቸው በምርጫው እንዲሳተፍ ቅስቀሳውን ከአሁኑ መጀመር አለባቸው። እውነቴን ነው የምለው የሚቀጥለው ምርጫ የኢትዮጵያን ህዝብ ለድል እንዲያበቃ ከተፈለገ እድሉ ያለው በነኚህ በሁለቱ ድርጅቶች ላይ ነው። ነገር ግን አንዱ አንዱን በመዝለፍ ህዝብን ሊከፋፍል በሚችል መንገድ አሸንፋለሁ ተብሎ ከታሰበ፤ መቼም ውጤቱን ለማወቅ ጠንቋይ መሆን አያስፈልግም። ውጤቱ እያው እንደተለመደው መፈረካከስን ነው የሚያስከትለው። የኢትዮጵያንም ህልፈተ ህይወት ያሳጥረዋል የሚል ስጋት አለኝ። መሪዎቹም እዬ አይነቱ ነገር እንዳይከሰት ጥንቃቄ በተሞላበት መንገድ ትግላቸውን ያፋፍሙት ዝንድ ከወገቤ በርከክ ብዬ ልመናዬን አቀርባልሁ።

ሕዝቅያስ ፍቅሬ
AGERE_ETHIOPIAA@yahoo.com